# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 36

ጥቅምት 13 ቀን 2015ዓም(23-10-2022)

በዚህ ሳምንታዊ ቅንብራችን የምናቀርበው የተለዬ ነገር ባይኖርም በአብይ አህመድ መንግሥትና በተባበሩት መንግሥታት ማለትም የአውሮፓውያንና የአሜሪካ ጥላና ጉዳይ አስፈጻሚ በሆነው ድርጅት በኩል የተነሳውን በዓላማ ያልተለያዬ ግን በወሳኝነት ድርሻ የተነሳ በአገራችን ላይ ሊቃጣ ያንዣበበውን የመበታተን አደጋና ወረራ የሚመለከት ይሆናል።በዓላማ ያልተለያዬ ያልንበት ምክንያትም አብይ አህመድ ሕዝብ አንቅሮ የተፋውን የወያኔ አገዛዝ ተክቶ የምዕራቡን ፍላጎት ለማስፈጸም ታጭቶ ለሰላም የቆመ ተደርጎ የተሸለመ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።አሁንም ቢሆን ዳር ዳር የሚለው የሕዝቡን ቁጣ ለማብረድ እንጂ እውነት ከወያኔዎችና ከምዕራቡ ፍላጎት የተለዬ አቋም ኖሮት አይደለም።አብይ የሚመራው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥትም ሆነ ወያኔዎችና ምዕራባውያን ችግሩ በሕገመንግሥቱ መሰረት ይፈታ የሚለው የጋራ ፍላጎታቸው የሚያስማማና የሚያቀራርባቸው ነው።ሁሉም ጠባቸው ከኢትዮጵያ አንድነትና ከኢትዮጵያውያን ጋር ስለሆነ ለዚያ መሣሪያቸው ሕገመንግሥት የሚሉት አገር አፍራሽ መመሪያቸው ነው።

ለውጭ አገሮች ጣልቃ ገብነት በር የከፈተውና ምክንያት የሆነው በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው ግን ለኢትዮጵያ ያልሆኑ ሰዎች በፈጠሩት ችግርና አገር የማፈራረስ ውድድር የመጣ ለመሆኑ እንኳንስ እኛ ቀርተን የሌላው አገር ተወላጅ የሚያውቀው ነው።ለዛም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ቅን አመለካከት ያላቸው፣የጎሳ ፖለቲካው ለነሱም ስጋት የሆነባቸው የውጭ አገር ዜጎች በተለይም የቅኝ ገዥዎችን አስከፊ ገጽ የቀመሱና ያወቁ ጥቂት የአፍሪካ ተወላጆች ችግሩ እንዲፈታ ካላቸው ፍላጎት ብዙ ምክርና ጥሪ አድርገዋል።ጥቅምና ሥልጣን ጆሯቸውን ብቻ ሳይሆን ልባቸውንም የደፈነው ፣በጎሳ ህሳቤ የተለከፉ የህወሃትና የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድኖች ግን ጦርነቱንና ቀውሱን የመጀመሪያና የመጨረሻ አማራጫቸው በማድረግ ለብዙ ሕዝብ ማለቅ፣መቁሰል፣ለአገር ሃብት መውደም ምክንያት የሆነውን ጦርነታቸውን የአቅም መለኪያና መፎካከሪያ አድርገው ቀጥለውበታል።ይህ ጦርነት በሕዝብና በአገር ስም የሚካሄድ የአምባገነኖች ጦርነት እንጂ የንጹህ ኢትዮጵያውያን ጦርነት አይደለም።ገና ከጅምሩ ሁለት ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ከይሲዎች የሚያካሂዱት ጦርነት መሆኑን ደጋግመን ገልጸናል። በቀውስ ውስጥ ተፈጥረው፣በቀውስ ውስጥ ያደጉ እነዚህ ከይሲዎች ከጦርነት ውጭ የሚያውቁት የለም።ለነሱ ሰላም ማለት አገር ተረጋግቶ ፣ሕዝብ ተስማምቶ ማደሩ ሳይሆን የነሱ የሥልጣንና የጥቅም ፍላጎት ሲከበር ብቻ ነው።

በዚህ ጉዟቸው በሃይልም በውሸትም ሕዝቡን እያስገደዱ የጦር ሲሳይ ያደርጉታል፤ሕዝቡም የነሱን ውሸትና ክፋት እያዬና እያወቀ እምቢ ከማለት ይልቅ ጭዳ መሆኑን የመረጠ ይመስላል። የትግራይ ተወላጅ ባለፉት የወያኔ አገዛዞች የደረሰበትን የመከራ ጊዜ ዘንግቶ በስሙ የነገዱበትን ጨካኞች አጅቦ በጦር ሜዳ እንደ ቅጠል እዬረገፈ ነው።በሌላውም በኩል እንዲሁ በማንነቱ እዬጨፈጨፈና እያፈናቀለ የሚፈጀውን የኦነግ ኢሕዴድ ብልጽግና የተባለ እኩይ ስብስብ አጅቦ ህይወቱን እዬገበረ ይገኛል።ይህንን በሚመለከት ከሰሞኑ በጎንደር ፣በባሕርዳርና በወላይታ ከተማዎች ያዬናቸው የአድርባይነት የመድረክ ላይ ውሎዎች ያረጋግጣሉ።ጎንደር ከፍለሃገር የአጤ ቴዎድሮስና የነገብርዬ ብቻ ሳይሆን እነ አገኘሁ ተሻገርን የመሳሰሉ የባንዳዎችም እትብት የተቀበረበት እንደሆነ፣ጎጃምም የበላይ ዘለቀ መፍለቂያ ብቻ ሳይሆን የነተመስገን ጥሩነህና መሰሎቹ የተወለዱበት መሬት መሆኑን፤ ደቡብም የነሃብተጊዮርጊስና

የአሁኑ የከተማው አርበኛ የታዲዎስ ታንቱ  ብቻ ሳይሆን የነአሰፋ፣ የርስቱ ላቀውና የሃይለማርያም ደሳለኝና የመሳሰሉት ወራዳዎች የበቀሉበት ክፍለሃገር መሆኑን ታዝበናል።

ለአገሩ ነጻነትና አንድነት ህይወቱን የሰጠው ቴዎድሮስ ተወልዶ ባለፈበት መሬት ላይ ኢትዮጵያን ለመበታተን የተዘጋጀና ጀግና አርበኞችንና ፋኖዎችን እያሳደደ የሚገድል፣የአማራውን አጽመ እርስት ቀምቶ ለወያኔ በመስጠት እንዲገነጠሉ በር ለመክፈት የሚሽቀዳደምና ሽርጉድ የሚል፣የአማራውን መጨፍጨፍ በስክጀርባ የሚመራውን ወንጀለኛና አጭበርባሪ የአነግ አሕዴድ ብልጽግና መሪ  አብይ አህመድን እንደ አገር ወዳድ ጀግና የአበባ እቅፍ ተሸክሞ፣በአዝማሪና በአሸብሻቢ፣በሽሆችና በቀሳውስት የታጀበ አቀባበል ሲያደርጉ ማዬትን የመሰለ የሚያም ነገር የለም።ከ15 ሽህ በላይ የአማራ ፋኖ አባላት በእስር ቤት ሲሰቃዩና የቀሩትም ሲሳደዱ እያዬና እዬሰማ ፣ ተጠያቂ የሆነውን አብይ አህመድን የጎንደር ተወላጅ የሆነ አድርባይ ሁላ ተሸክሞ ሲፎክርና ሲደልቅ ስናይ ቴዎድሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ሞቷል ለማለት እንደፍራለን።በተለይም እንደ ቴዎድሮስ ለብሶና ጸጉሩን ገምዶ በአድርባይነት የተሰለፈ የጎንደር ሰው ሲታይ ለጎንደሬ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም አማራ ሃፍረት ነው።ምነው ጎንደር የአድርባይና የባንዳ ዋሻ ሆነ?ወንዱ ብቻ ሳይሆን ሴቶቹም ሳይቀሩ የአምባገነኖች መጠቀሚያ መሆናቸው ምን ነካው ጎንደር ያሰኛል። የጎንደር ሴቶችን ያዋረዱት የመለስ ዜናዊ ሚስት የነበረችው አዜብ መስፍንና የአብይ አህመድም ሚስት ዝናሽ ለጎንደር ሴቶች ብቻም ሳይሆን ለጠቅቅላላው ኢትዮጵያውያን ሴቶች ማፈሪያዎች ናቸው።የነሱም ቤተሰቦች ታሪክ  ሲመረመር አብዛኞቹ የጣልያን ባንዳዎች የነበሩ መሆናቸው ተረጋግጧል።ሁለቱም ሴቶች በባንዳ አያትና  አጎቶቻቸው ቤት ያደጉ በመሆናቸው፣ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑት ጋር ውለው ማደራቸው  ለያዙት ጸረ ኢትዮጵያዊነት አቋም ሳይዳርጋቸው አልቀረም። አስተዳደጋቸው ከጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑት  ከመለስ ዜናዊና ከአብይ አህመድ ጎን ለመቆም፣ በጋብቻ ለመተሳሰር የመሰረት ድንጋይ ሆኗቸዋል።የዘሬን ባይ ያንዘርዝረኝ ነው።ወይም ፍሬ ከዛፉ እርቆ አይወድቅም የሚለው ማለት ነው። ከስንዴ መካከል እንክርዳድ እንደማይጠፋ ሁሉ ከህብረተሰብም ውስጥ አርበኛና ባንዳ አይጠፋም።ታሪካችንም ያንኑ ይመሰክራል።ጊዜው በተለወጠ ቁጥር ባንዳዎቹ ተለወጡ እንጂ ባንዳነት አልተለወጠም።በባንዳዎች ላይ ተገቢ ቅጣት ካልተወሰደ በቀር ባንዳ በዬወቅቱ ብቅ ማለቱ አይቀርም።

አብይ አህመድ በመጀመሪያ በባሕርዳር ውስጥ ከዚያም በጎንደር የሚያካሂደውን የአጭር ጊዜ ታይታ ፈጽሞ ያመራው ወደ ደቡብ ነበር ።በዚህም ጉዞው በወላይታ ውስጥ እንዲሁ የአድርባዮችና የተጠቃሚዎቹ ጎራ በሜዳና በአዳራሽ ውስጥ ተጠቅጥቆ ድጋፍና ታማኝነቱን ገልጿል።እውነተኛውን የሕዝቡን ጥያቄ በማድበስበስ ለነሱ የሚተርፍ ጥቅም ተፋሰስ እንዲደረግ የሚረዱ ጥያቄዎችን በማንሳት አቤቱታ አይሉት ምስጋና የአብይ አህመድን መምጣት እንደ ትልቅ ሎተሪ ዕድል በመቁጠር በቃላት የታጀበ ደጅ ጥናት ሲያደርጉ ታይቷል። እንደማንኛውም ጊዜ አብይ አህመድ የሕዝቡን ስስ ብልት እዬፈለገ ለማማለል ሞክሯል።በአካባቢው ቋንቋ አንዳንድ ቃላት እዬወረወረ፣ውዳሴና ምስጋና እያቀረበ የሚፈልገውን ለማለት አልተቸገረም።የዋሁም እውነት እዬመሰለው እጁ እስኪላጥ ድረስ እያጨበጨበ ሞቅ አድርጎታል። ባደረገው ንግግር ሁለት የማይናቁ የጥፋት መልእክቶችንም ጣል ጣል አድርጓል።

አንደኛው የወላይታ ሕዝብ በኢትዮጵያ እንደተበደለ አድርጎ ያቀረበበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የወላይታ ሕዝብ ለትግራይ መጨነቅ እንደሌለበት ፣የእኔም ነው ብሎ እንዳያስብ የተናገረው መልእክት ነው።

ወደ መጀመሪያው አባባሉ ስንገባና ስንፈትሸው።የወላይታ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ያገኘው ነገር የለም፣ግን ኢትዮጵያ እያለ በጦርሜዳ ብዙ መከራ ተቀብሏል። ኢትዮጵያ ካደረገችለት ይልቅ እሱ ለኢትዮጵያ

ያደረገው ይበልጣል ብሏል። ይህም ማለት በተዘወርዋሪ ላልሆነችላችሁ አገር አትጨነቁ የሚል ነው። ሁሉም ሕዝብ የተሰቃዬውና መከራ ያዬው በነበሩትና አሁንም እሱ በሚመራው ስርዓት መሆኑ ሲታወቅ ኢትዮጵያ ያደረሰችበት ግፍና መከራ ነው ብሎ ማቅረቡ የወላይታ ሕዝብ ስለኢትዮጵያ ያለውን ፍቅርና ክብር ለመናድ ታስቦ ያደረገው ከይሲ አካሄድ ነው እንላለን።እነታዲዎስ ታንቱን የመሰሉ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑና የሚታገሉ ሰዎችን ያበቀለች የወላይታ መሬት ሕዝብ በዚህ ተራ ተንኮል ተማርኮ ኢትዮጵያዊነቱን አሽቀንጥሮ እንደማይጥል እናምናለን። በሁለተኛው መልእክቱ ደግሞ ከመጀመሪያው ጋር የተያያዘ ሆኖ የትግራይን መገንጠል እንዲቀበል ያደረገበት ስውር መልእክቱ ነው፣ያንንም ለወላይታ ድንበሩ በምዕራብ ደቡብ የጋምቤላ ጫፍ፤በምሥራቁ የሶማሊያ ድንበር፣በሰሜን የተከዜ ወንዝ ድረስ ነው ሲል እቅጩን ነግሮታል።ይህ ማለት ከተከዜ ወዲያ ያለው መሬት የኢትዮጵያ መሬት፣ ሕዝቡም ኢትዮጵያዊ አይደለም ማለት ነው።ይህንን አባባሉን ወደ ተግባር ስንተረጉመው ትግራይ ለመገንጠል ሕገመንግስታዊ መብት አለው ፤ይሂድ ማለት ነው።ቢገነጠል ወላይታን የሚያገባው አይደለም ማለቱ ነው።በተደጋጋሚ የወልቃይትም ሆነ የራያና አዘቦ ጥያቄ ወያኔ በሚፈልገው መንገድ በሕገመንግሥቱ መሰረት ይፈታል የሚለው አቋሙ ከዚህ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው! የሚገርመው ነገር በደቡብ በኩል የወላይታ ድንበሩ እስከዬት እንደሆነ አለመግለጹ ነው።ለምን ቢባል በሲዳሞ ደቡብ ከኬንያ ጋር የሚዋሰንበት መሬት የነገሌ ቦረና ስለሆነ ያንን ለመግለጽ ያልፈለገው የራሱ ድርጅት ኦነግ የኦሮሚያ ለሚለው የሕልም አገር የግዛት ክልሌ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው።ስለሆነም ወላይታን ወይም የደቡብ ክልልን ስለ ነገሌ ቦረና አያገባውም ማለት ነው።ይህንን ሁሉ መርዘኛ መልእክት ሲረጭ በግርግር ክልል ሆነን እንጠቀማለን ብለው ያሰፈሰፉት የወላይታ ጥቅመኞች በታላቅ ደስታ የተቀበሉት መሆኑን በሚያሰሙት ጭብጨባ ለመታዘብ ችለናል።

በጥቅመኞቹ በኩል ለቀረቡት የክልልና የልማት ጥያቄ ሲመልስ ግን እንደሚጠብቁት አልሆነላቸውም። ክልል ሆነን የገንዘብ (ባጀት) ይመጣልናል ብላችሁ አትጠብቁ፣ምንም ገንዘብ የለም፣የኢንዱስተሪ ፓርክም ይከፈትልናል ብላችሁ አትጓጉ፤ የተከፈቱትም ቢሆኑ ኪሳራ እንጂ ጥቅም አላመጡም ፣ እርማችሁን አውጡ፣የምንችለውን ለማድረግ እንሞክራለን ፤ሁሉንም ጥያቄያችሁን ልንመልስ አንችልም፤ፈጣሪ እንዲመልስላችሁ አጥብቃችሁ ጸልዩ ሲል እቅጩን ነግሯቸዋል።ተጠያቂው እርሱ የሚመራው መንግሥት ሳይሆን ፈጣሪ መሆኑን እዬሳቀ አጃጅሏቸዋል። መንግሥት በመሬቱ ላይ ያለበትን ኣላፊነት ወደ ፈጣሪ በመወርወር ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሞክሯል።የወላይታ ሕዝብ በዚህ መርካቱን ወይም አለመርካቱን የምናዬው ይሆናል።እርግጠኞች ሆነን የምንናገረው ቢኖር የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ በወላይታ ተወላጆች ላይ ብቻም ሳይሆን በሁሉም ጎሳ ተወላጆች ላይ የሚደርሰው በደል ይበልጥ እያደገ ይሄዳል እንጂ እዬቀነሰ አይመጣም።ያ ደግሞ ይዋል ይደር እንጂ ሁሉንም ለሕዝባዊ አመጽ መቀስቀሱ አይቀርም።የጊዜ ጉዳይ ነው።

በሰሞኑ የደቡብ ተወላጆች ብቅ ብለው የመሰከሩት ቢኖር ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አማራውን ከጨፈጨፈ በኋላ ሌላውንም ጎሳ እንደማይምረው ያመላከተ ማስረጃ ነበር።በሚድያ ለመቅረብ ዕድል ያገኙት የደቡብ ሰዎች ሲናገሩ እኛ እናንተን አንነካም፣እናንተ የእኛ ወገኖች ናችሁ፤የምንጨፈጭፈው አማራውን ብቻ ነው ብለውን አይነኩንም ብለን ስንዝናና አማራውን ከጨፈጨፉ በኋላ እኛን በተናጠል ስላገኙን ጨፈጨፉን፣ንብረታችንን ዘረፉ፤አፈናቀሉን ሲሉ የሰጡት የእምነት ቃል እኛ ባለፉት ጊዜያቶች ሊሆን እንደሚችል በተደጋጋሚ ያሰማነውን መልእክት እውነትነት የሚያረጋግጥ ሆኗል። በአማራው ጉዳትና ስቃይ እጠቀማለሁ፣እኔ ከኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ጭፍጨፋና እልቂት እድናለሁ የሚል እንደ እርስቱ ይርዳው ያለ እንከፍ አድርባይና እራስ ወዳድ ከዚህ ሊማር ይገባዋል

እንላለን።ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የመሬትና የሃብት ፍቅር እንጂ ለሰውና ለአገር ፍቅር እንደሌለው ከዚህ በላይ ማስረጃ የለም።ልብ ያለው ልብ ይበል!

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተብዬውም ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ ሊኖራቸው የሚፈልጉትን ተጽእኖ ለማስከበር ሲል ታማኝ አገልጋዮቻቸው በሆኑት በወያኔዎቹ ጀርባ በመሰለፍ ለሰላምና ለሕዝቡ የቆመ በመምሰል የማስገደድ እርምጃውን በማጠናከር ላይ ነው። በዓለም ባንክና በዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም በኩል የሚያደርጉት ተጽእኖ የዚያው አካል ነው። ምዕራባውያን በአፍሪካ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ሊኖራቸው የሚፈልጉትን የበላይነት በቻይናዎችና በሩስያኖች እያጡ መምጣታቸው እንቅልፍ ስለነሳቸው እንጂ የኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ አሳዝኗቸው አይደለም። በማዕቀብ ላይ ማዕቀብ ለመጣልና ከዚያም አልፎ ተርፎ የሰላም አስከባሪ በሚል ሰበብ ያገራችንን ልዑላዊነት ለመዳፈር ዕቅድ በማውጣት ላይ ናቸው።በዚህ ወረራ ሁሉም የሚጎዳ እንጂ የሚጠቀም አይኖርም።ለትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያውያን በላይ ነጮች አይቀርቡትም፣አያስቡለትም። እንኳንስ ነጮቹ የራሱም ልጆች የሆኑት ህውሃቶች አያስቡለትም።ለ27 ዓመታት በሥልጣን ላይ በቆዩበት ጊዜ በስሙ ነገዱበት እንጂ ደሃው የትግራይ ሕዝብ ከነበረበት የድህነት ኑሮ ፈቀቅ አላለም። ላንተ ቆመናል እያሉ ጥቂቶቹ የወያኔ መሪዎችና አጋሮቻቸው ተጠቅመውበታል፤የሃብትና የንብረት ባለቤቶች ሆነውበታል፣ቤተሰብና ልጆቻቸውን የተሞላቀቀ ኑሮ በአገርና በውጭ አገር እንዲኖሩ አድርገዋል። ለትግራይ ሕዝብ የተረፈው ነገር ቢኖር ለነሱ ጥቅምና ሥልጣን በሚጭሩት ጦርነት መማገድና ህይወቱን መገበር ብቻ ነው።በባዶ የትግራይ ማንነት እያማለሉ ለጥፋት እልህ ውስጥ እንዲገባ መቀስቀስና ከመሰል ወገኑ ጋር ደም እንዲቃባ ሆነ እንጂ ከርሃብና ከስደት አልወጣም።በዚህ ከቀጠለም ይበልጥ ይሰቃያል እንጂ የተሻለ ኑሮ ባለቤት አይሆንም።ወያኔዎች እያስተዳደሩ በኖሩባት በሰፊዋ ኢትዮጵያ ያላገኘውን ድሎት ወያኔዎች ገንጥለው እንመሠርታለን በሚሏት በጠባቧ ትግራይ ውስጥ ተጨናንቆ ከመኖር የተሻለ ኑሮ አገኛለሁ ማለት ዘበት ነው።ከድጡ ወደማጡ ወይም ከምጣዱ ወደ እሳቱ መውደቅ ይሆናል።ያለው ምርጫ በስሙ የሚነግዱበትንና ለስቃይ ኑሮና ለእልቂት የዳረጉትን የወያኔ መሪዎች ከጫንቃው ላይ አውርዶ ከቀሪው ወገኑ ከኢትዮጵያውያን ጋር ሆኖ የጎሰኞቹን ስርዓት አሶግዶ ሕዝባዊ ስርዓት መመስረት ብቻ ነው።

በምዕራባውያን የሚቀነቀነው የሰላም ድርድር ዋናው ዓላማ ወያኔና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ተስማምተው የአሸከርነት ሚናቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ሲሆን ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው የድርድር ሂደትም ላይ አውሮፓውያኑ የፈላጭ ቆራጭነት ሚና ይኑረን በማለት ምክንያት ከሁለት ሳምንት በፊት ሊደረግ የነበረው ድርድር ሳይካሄድ መቅረቱ የሚታወስ ነው ።አሁንም በነገው እለት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ይካሄዳል የተባለው ድርድር የአውሮፓውያንን ፍላጎት የሚያስከብር ከመሆን ያለፈ አይሆንም።ያ ካልሆነላቸው ባቀዱት ኢትዮጵያን የመበታተን ሂደት ውስጥ ለመግባት አያቅማሙም።

ዓይን ያወጣው የጣልቃ ገብነታቸው ደረጃ መንግሥት አለ በሚባልባት ኢትዮጵያ ውስጥ በዕርዳታ ሽፋን እንደልብ እዬገቡ እዬወጡ ወያኔን ለማዳን ያደረጉት ሳያንስ፣ አሁን ይባስ ብለው በድርድር ስም አሜሪካኖች የወያኔን ቡድን ለማጓጓዝ መቀሌ የሚገባ አውሮፕላን ጅቡቲ ከሚገኘው የጦር ሰፈራቸው ማዘጋጀታቸው ነው።ከዚህ በላይ ዓይን ያወጣ ጣልቃ ገብነት የለም።ነገ ደግሞ ጅቡቲ የሰፈረውን ጦራቸውን በሰላም አስከባሪ ስም የማያስማሩበት ድፍረት አይኖርም።ምዕራባውያንን በተለይም አሜሪካንን የዴሞክራሲና የሰላም ብሎም የሰብአዊ መብት አስከባሪና ተቆርቋሪ አድርገህ የምታይ የዋህ ከዚህ ተማር! የምዕራባውያን አፈ ቀላጤ የሆንክም ከዚህ ተማር!በሌሎች አገሮች ካደረሱት ተመሳሳይ ውድቀት ተማር!በታሪክ እንዳትወቀስ እንደ አያት አባቶችህ ለአገር ነጻነትና ልዑላዊነት ቁም።

የሰው ወርቅ አያደምቅ ነውና በስደት  በምታገኘው ጥቅምና ብልጭልጭ ኑሮ እራስህን አትሸጥ!ለብዙ ዓመታት አብሮ ለኖራቸው፣አገሪቱን በደምና በአጥንቱ ለገነባው  ለጥቁር አፍሪካ  አሜሪካኖች፣ ለህንዶችና ስፓኒሾች፣ ያልሆነች አሜሪካ ከሃምሳ ዓመት ወዲህ በስደት ለገባኸው ኢትዮጵያዊ ትሆነኛለች ብለህ ለወራሪዎች ጥብቅና አትቁም።ቀደም ሲል የኮሪያን፣የቬትናምን፣የላኦስን፣አሁንም የሶሪን፣የሊቢያንና የዬመንን ውድቀት አስብ! በአገርህ ላይ የሚደረገውን ደባ ለዴሞክራሲ ለውጥና መከበር ነው ብለህ በዝምታ አትለፍ!እራስህን አታታል።በአድዋ ጦር ሜዳ  የታሪክ ውርደት ላደረሰችባቸው፣ለሌላው ቅኝ ግዛት ሕዝብ የአርነት ትግል ፋና ወጊ ለሆነችባቸው ኢትዮጵያ ያዝናሉ፣ ይራራሉ ብለህ አታስብ!ተቆራርሳ እንድትበታተን የሚሸርቡትን ተንኮል ተረዳ!ጅጅጋን ከሞቃዲሾ፣ አፋርን ከጅቡቲ፣ቦረናን ከኬንያ፣ጋምቤላን ከደቡብ ሱዳን ለማቀላቀል፣ትግራይንና ኦሮሚያን ነጻ አገሮች ለማድረግ  የሚደረገውን ሴራ አጢን ።የደቡብ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ የሚቀራመቱህ ቅርጫ መሆንህን አስብ!የሚቆራርሱህ በቀላሉ ሊውጡህ እንደሆነ ተረዳ!

አገሩን ለማዳን መስሎት ህይወቱን የሚገብረው ኢትዮጵያዊ በሁለት ወሮበሎች መካከል ለሚደረገው የሥልጣንና የጥቅም ጦርነት እራሱን ከመማገድ ይልቅ ፣በነሱ ላይ በመነሳት የጦርነቱን ዕድሜ ማሳጠር ይኖርበታል።ህወሃትና የኦነግ ኦህዴድ ብልጽግና  ቡድኖች በህይወት እስካሉ ድረስ ሰላምና አንድነት ይኖራል ማለት ዘበት ነው።ከዚያም አልፎ ተርፎ ኢትዮጵያ እንደ አገር ዳር ድንበሯን አስከብራ የመኖር ዕድሏ የመነመነ ነው።

ፊደል የቆጠረው ዜጋ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ደጋግመን አሳስበናል።አሁንም ቢሆን አገርን ለመታደግ  የአላፊነት ሚና ሊጫወት ይገባል።ጉንጭ አልፋ ወሬ በዬስብሰባውና በዬሚዲያው ላይ እያናፈሰ ጊዜውን ከሚያጠፋ ይልቅ እራሱን በአንድ ድርጅት ሰብስቦ ሌላውን ለመሰብሰብ መጣር ይኖርበታል።ትግል ያለድርጅት ድካም እንጂ ውጤት የለውም።አገር አፍራሾቹ  ቡድኖች የሚንቀሳቀሱት ተደራጅተው ነው።እነሱን ለመቋቋምም ያለው ትልቁ መሣሪያ  ከነሱ በተሻለ መልክ ተደራጅቶ መገኘት ነው።እስከዛሬ ድረስ ትግሉ ውጤት ያላመጣው መስዋእትነት ሳይከፈልና ሳይታገሉ ቀርቶ ሳይሆን ጠንካራ ድርጅት ባለመፍጠሩ ነው።እርግጥ ነው በድርጅት ስም ለቁጥር የሚያታክቱ ሜዳውን  ሞልተውታል።እኛ ድርጅት ስንል እንደነሱ በአድር ባይነት የተጨማለቁትንና ለሥልጣን ቋምጠው የሚሮጡትን  ማለታችን አይደለም። ለአገራቸው አንድነት፣ለሕዝባቸው ክብርና፣መብት ሳይፈሩና ሳይግደረደሩ፣ያለውን አገር አጥፊ የጎሰኞች ስርዓት ለማሶገድ የሚታገሉበት፣ለውጭ ሃይሎች ያላጎበደዱ የሚመሩት የአገር ወዳዶች ድርጅት ማለታችን ነው።

ለአገር አንድነትና  ለዜጎች መብት ሲሉ እራሳቸውን ለመከራ አጋልጠው በዬእስር ቤቱ የሚማቅቁትን ፣ ተመስገን ደሳለኝን፣ታዲዎስ ታንቱን፣ጎበዜ ሲሳይንና ሌሎቹንም ጋዜጠኞችና አንቂዎች፣የሙብት ተከራካሪዎችና የፖለቲካ ድርጅት አባላት ፣እንዲሁም ለአማራው ደህንነት ሲሉ ለትግል ተሰልፈው ያሉትን የአማራ  ፋኖና ልዩ ሃይል አባላትን በሆነ ባልሆነው ውንጀላ ብእዴን በተባለው ጭቃ ሹም ፊታውራሪነት ማፈንና ማሳደድ እንዲቆም፣የታሰሩት እንዲፈቱ መጠዬቅ ወይም በጉልበት ነጻ ማድረግ የሁሉም አገር ወዳድ ድርሻ ነው እንላለን።በራሱ ጨካኞች ላይ ዘምቶ ሙብቱን ለማረጋገጥ ያልቻለ የምዕራቡን ወረራ ይቋቋማል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው።ከሁሉም መጀመሪያ የራስን ቁሻሻ ማጽዳት ይቀድማል።

በትናንትናው  ቅዳሜ ዕለት በጥቅምት 12 ቀን ያዬነው በመንግሥት የተዘጋጀ ሰላማው ሰልፍ ሲደረግ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ።በደርግ ዘመን በልጆቹ አስከሬን ላይ ቆሞ ከደርግ ጋር ወደፊት እያለ ለሰልፍ  የወጣ ነበር።በወያኔ ቁጥር አንድም በኢሕዴግ ጊዜ በሚያዝያ 29 ቀን 1997 ዓም እንዲሁ ወያኔን ደግፎ የወጣ ሕዝብ ነበር።በማግሥቱም ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓም ቅንጅት በሚባለው

የተቃዋሚ ስብስብ ጥሪ  ወያኔ ኢሕአዴግን ተቃውሞ የወጣ መኖሩን እናስታውሳለን።አሁንም ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናን ደግፎ ቢወጣ የሚያስገርም አይደለም።ሕዝብ መንጋ  ነው መንጋ በእረኛው ፈቃድና ፍላጎት እንደሚሰማራ ሁሉ ለጥፋትም ሆነ ለልማት የተሰለፈ እረኛ የሆነ መንግሥትም ሆነ ድርጅት በሚፈልግበት መንገድ ይነዳዋል። ስልጣን ላይ የተቀመጠን ቡድን ደግፎ መሰለፉአዲስ ተአምር አይደለም።ነገ ደግሞ የተለዬ ሃይል ለሰልፍ ቢጠራው እምቢ አይልም።ችግሩ እንደ ቅንጅት መንግሥትን የሚቃወም ጠንካራና ደፋር ድርጅት አለመኖሩ ብቻ ነው።የትናንትናዎቹም የቅንጅት መሪዎች ዛሬ በደል የሚፈጽመው የጎሰኞች ስብስብ የሆነው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አሽከሮች ሆነዋል።ከአብይ ኋላ ቦርሳ ተሸክመው እንከፍ እንከፍ ይላሉ።

በአዲስ አበባ ሰልፍ ሲደረግ አብይ አህመድ እንደልማዱ የለሁበትም ለማለት በጉብኝትና በምረቃ ሽፋን ጂማ ገብቷል።በዚያ ጉዞው አሽቃባጮቹን ብቻ ሳይሆን ማንነታቸው ያልታወቀ  ፈረንጆችንም ይዞ መሄዱን ታዝበናል።በአዲስ አበባ በተደረገው ሰልፍ ላይ እንደ ጃንጥራርና ደበበ እሸቱን  ያሉትን ተላላኪ ውሻዎቹን በምዕራቡ ላይ እንዲጮሁ በማዘዝ እራሱን ነጻ ለማድረግ ሞክሯል።ጃንጥራርም ምዕራባውያንን ገንዘባችሁን እንጂ ነቀፌታና ሴራችሁን አንሻም በማለት ከአጥንቱ ጾመኛ ነኝ ከመረቁ ግን አድርጉልኝ መሳይ ይሉኝታቢስ አባባሉን በአደባባይ ዘርግፎታል። እርዳታና ድጋፋችሁን ብትሰጡን ከወያኔ በላይ ታማኝ አገልጋይ እንሆናለን የሚል መልእክቱን በሽፍንፍን አስተላልፏል።

ጣልቃ ገብነትን እቃወማለሁ ማለት በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በኤኮኖሚና በባህልም መስክ ውስጥ ጣልቃ መግባትንም ያጠቃልላል። ለጃንጥራር ይህ ግልጽ የሆነለት አይመስልም።የፖለቲካ ጥቅም መረማመጃው እርዳታ እንደሆነ አላወቀም።ምዕራባውያን ሲረዱ በምላሹ  ለሚያገኙት ጥቅም ሲሉ እንጂ ለሰማይ ቤት አይደለም። በንግግሩ ወያኔ ወይም ጁንታው የአገራችንን አንድነት ለመቦርቦር የተሰለፈ ነው ሲል እራሱ የተሳተፈበት የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥት በወያኔ ሕገመንግሥትና የጎሳ ፖለቲካ ውስጥ መነከሩን የዘነጋው ይመስላል። የወያኔ ቁጥር ሁለት መሆኑን ስቶታል።ወይም ሰልፍ የወጣው መንጋ የማሰብ ችሎታ የለውምና ላሙኛችሁ ዓይናችሁን ጨፍኑ ብል የሚጠይቀኝ የለም የሚል ድፍረት አድርቦበት ይሆናል።

የኪነት ባለሙያዎችን  ወክሎ የተናገረው ደበበ እሸቱ  በምዕራባውያን ላይ ያሰማውን ነቀፋ ብዙዎቻችን የምንቀበለው ሲሆን በመንግሥት ላይ ግን ደጋፊ እንደመሆኑ መጠን የቀውሱ ተጠያቂ መሆኑን አምኖ  ለመቃወም ድፍረትና ጀግንነት አልታዩበትም፤አይጠበቅበትም። ታማኝነቱን በዴሞክራሲ የተመረጠ መንግሥት ሲል እንደልማዱ  ባደባባይ ደግሞታል።በሚያደርገው ተደጋጋሚ አድር ባይነት ቢመከር ቢመከር ባለመስማቱ ደበበን ደደበ ማለቱ ሳይሻል አይቀርም።

ብልጽግና ሰልፉን ያዘጋጀው  ለታይታና ለማስመሰል  እንጂ  ካለው ጸረ ኢትዮጵያ አቋምና አፈጣጠር ከልቡ የወያኔዎች ጸር ሆኖ አይደለም።፣ለምዕራባውያንም ካለው ፍቅርና የባርነት ስሜት ያፈነገጠ  አገር ወዳድ ሆኖ አይደለም።ነጮቹም በሚገባ ያውቁታል። ከላይ እንደገለጽነው አንድ ሕዝባዊ ጠንካራ ድርጅት ቢኖርና የተቃውሞ ሰልፍ ቢጠራ ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ከጠራው ሰልፍ ተሳታፊ የእጥፍ እጥፍ የሆነ ሕዝብ በተሰለፈና ዳግማዊ ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓም በተደገመ ነበር።

በቀጣዩ ቀን በዛሬው ጥቅምት 13 ቀን በሌሎቹ ክፍላተሃገር በተለይም በጎንደር፣በደብረብርሃንና በሌሎቹ ከተሞች በመንግሥት የተዘጋጀ ተመሳሳይ ሰልፍ ተካሂዷል።ሰልፉ አንድ አይነት መልክና ይዘት አለመኖሩንም ታዝበናል።በጎንደር የሩስያ ባንዲራ ሳይቀር የአብይ አህመድን ፎቶ ተሸክሞ የወጣ ፣ በባሕርዳር  ወያኔን እያወገዘ ግን ወያኔ ሰፍቶ የሰጠውን ባንዲራ ተሸክሞ የሚጮህ ሰልፈኛ አይተናል።

አንድ የተቃዋሚ ድርጅትና አመራር ቢኖር እንዲህ አይነቱ ዝብርቅርቅ ያለና  አስነዋሪ ሰልፍ ባልታዬም ነበር።

ሕዝብ ምዕራባውያንን እንዲቃወም ሲደረግ የአነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥት ግን ከዓላማው ዝንፍ ሳይል በዘረጋው እቅድ እዬተጓዘ መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የኦነግን ባንዲራና መዝሙር በሚመለከተው የከተማዋ አስተዳደር በዬትምህርት ቤቱ  ስብሰባ እንዲካሄድና ውሳኔውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ  ባስተላለፈው ትዕዛዝ  መሰረት መምህራንና ተማሪዎች እምቢተኛነታቸውን ቢገልጹም በግድ መፈጸም እንዳለባቸው እምቢ ባሉት ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ መገለጹን ሰምተናል።እንዲህ አይነቱ የተረኞችና የጎሰኞች ስርዓት ነው ኢትዮጵያን ከውጭ ወረራና ተጽእኖ አድናለሁ፣አንድነቷን አስከብራለሁ፣የሕዝቡን ነጻነትና እኩልነት አረጋግጣለሁ፤ተረኝነትንና ጎሰኝነትን እቃወማለሁ  ብሎ በሰልፍና በድግስ ለማምታታት የሚሞከረው።አዎ ! ባዶ ቤት በቁንጫ ይወረራል ! ባለቤት የሌለውም አገርም እንዲሁ የሚደፍረው ብዙ ነው፤የማንም መቀለጃ ይሆናል፣ከዛም አልፎ ተርፎ ይበታተናል።

አሁን የሰሜኑ ጦርነት መቋጫ ላይ መድረሱ በጥምር ጦሩ የበላይነት የትግራይን መሬት በአብዛኛው መቀሌ ብቻ ስትቀር መቆጣጠሩ እዬተወራ  አብይ አህመድ በተዘዋዋሪ ለምዕራባውያን በላከው መልእክቱ ጦርነቱ እንደሚቆምና ሰላም እንደሚወርድ  ቃል ገብቷል።የሰሜኑም ጦርነት በድል እንዳይጠናቀቅ  ለማቆም ዳር ዳር እያለ መሆኑ ተሰምቷል።መቀሌንም ከቦ የመደራደር አቅሙን ለማጎልበት እንጂ ወያኔን ለመደምሰስ የመወሰን ፍላጎት ያለው አይመስልም፤በማንኛውም ወቅት ጥምር ጦሩን ከትግራይ ለቃችሁ ውጡ ላለማለቱ ዋስትና  የለም። በደቡብ አፍሪካም በአደራዳሪዎቹና በምዕራባውያን በኩል  የድርድር ቅድመሁኔታ ሆኖ ስለቀረበ ይህንን ተግባራዊ አድርጎ እንደሚቀርብ ከወዲሁ ምልክቶች እዬታዩ ነው።በሥልጣኑ ላይ ጥያቄ ካልተነሳና እውቅና ካገኘ ለወያኔ የሚፈልገውን ከመስጠት ለምዕራብያውያኑም እንዲሁ የሚፈልጉትን የበላይነት ሚና ከማስከበር ወደኋላ አይልም። በተለይም አማራው የድርድሩ አካል ይሁን የሚለው ጥያቄ እያስተጋባ በመምጣቱ፣አማራው ለዚያ ከበቃ የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የበላይነት ማከተሙን የተረዳው አብይ አህመድ በአማራው መቃብር ላይ የማይደራደርበት ምክንያት አይኖርም።የአማራ ፋኖ ን እያሳደደ የኦነግና የጁዋር ሞሃመድን ጣምራ ጩፍጫፊ ጦር  እያበረታታ መሄዱ ለዚያ ማረጋገጫ ነው። አብይ አህመድ ለሚመራው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና  ከወያኔ በላይ ጠላቴ ነው የሚለው የአማራው ህብረተሰብ በመሆኑ እንዲደራጅና አንገቱን ቀና እንዲያደርግ አይሻም።በአገር ውስጥ እያስጨፈጨፈ በውጭ አገርም በሚካሄደው ድርድር ውስጥ እንዳይሳተፍ ያደርጋል። ያሉትን ተቀብሎ መፈራረሙ እንደማይቀር እርግጠኞች ነን።  ለማንኛውም የድርድሩን ውጤት ከሰኞ በኋላ የምናዬው ይሆናል።

ወጣም ወረደም ኢትዮጵያውያን ያለን አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው።ያገራችንን ህልውና ለማስከበር የእኛንም መብትና ነጻነት ለማረጋገጥ በሚያስችለን ትግል ውስጥ ገብተን ጠላቶቻችንን ድል ስናደርግ ብቻ ነው።

ወያኔ፣ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና፣ጸረ ኢትዮጵያ ምዕራባውያን አንድም ሁለትም ሦስትም ናቸው!!ከነሱ መዳፍ የሚያላቅቅና ነጻነታችንን የሚያስከብር ትግላችንን የሚመራ አገር ወዳድ ግንባር ይቋቋም!!!

እውነተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ ይፋፋም!!